# አቦይ ስብሀት አሁንም ተናግረዋል፤

# ሰሚ ካለም መፍትሄ አመላክተዋል

ኤርሚያስ ከአዲስ አበባ 01-11-17

የታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም የአዲስ ዘመን ጋዜጣን ለማንበብ የጓጓሁት ከሳምንት በፊት ታህሰስ 19 ላይ በወጣው አንድ ዜና ምክንያት ነበር። ዜናው በአቶ ስብሀት ነጋ ምንጭነት የተሰራና የኢህአዴግ ጉባኤ አሰራሩ እንዲፈተሽ አቶ ስብሀት ነጋ አመለከቱ የሚለው ነው። በዚህ ዜና ላይ አቶ ስብሀት ጉባኤው ለምን ሊፈተሽ ይገባል እንዳሉም ብቻ ሳይሆን ምን መሆን እንደሚገባውም አማራጭ ያቀረቡበትም ጭምር ነበር። በተጨማሪም ሌሎች ጉዳዮችን አንጋፋው የኢህአዴግ ሰው ጠቃቅሰዋል።

ከዚህ ዜና መውጣት በኋላ ጋዜጣው ሙሉ ቃለ መጠይቁን ሳምንት ይዞ እንደሚቀርብ ገልጿል። እዚህ ላይ ግን ጉጉትና ስጋት ተፈጥሮብኝ ነበር። ጉጉቴ አቦይ ስብሀት ያመኑበትን የሚናገሩ ምንም የሚፈሩት ነገር የሌለ ሰው ስለሆኑ ስለ ስርዓቱና ወቅታዊው የአገሪቷ ጉዳይ ምን ብለው ይሆን? የሚለው ነው። ስጋቴ ደግሞ ጋዜጣው አዲስ ዘመን ነውና በአርትኦት ቆርጦ ቢያስቀረውስ? የሚለው ነው። ሁለቱም ግን ሳምንቱ ደርሶ ተመለከትኩና ይሄንን ለመጻፍ ወሰንኩ።

ጉጉቴ በትክክልም ትክክል ነበር። አቦይ ስብሀት እንደጠበኩት ነገሮችን ፍርጥርጥ አድርገው ተናግረዋል። ስጋቴ ግን ትክክል አልነበረም፤ አዲስ ዘመን የአቦይን ንግግር ሳይቆርጥ እንደወረደ አቅርቦልናል። ወይንም እንዳቀረበው ነገሮናል። ያም ሆነ ይህ ግን በዚህ ቃለ መጠይቅ ዙሪያ የተሰሙኝንና እንደ ዜጋ የሚመለከተኝንም ብቻ ሳይሆን ያገባኛል ያልኩትንም ጭምር በዚሁ ጋዜጣ ላይ መጻፍ ወደድኩ።

አዲስ ዘመን በዚህ ደረጃ የአቦይ ስብሀትን ቃለ መጠይቅ ማውጣቱ ሳያስገርመኝ እንዳልቀረ ሳልጠቅስ ማለፉ ተገቢ አይደለም። ሁሉም ሰው እንደሚያስበው የመንግስት ሚዲያዎች የመንግስትንና የኢህአዴግን መልካም ነገሮች ማውጣት እንጂ፤ እንደዚህ አይነት ደፍሮ ሂስ የሚያሰጥንም ሆነ ጉድለትን የሚያሳዩ አመለካከቶችን የማስተናገድ ተሞክሯቸው ሲበዛ ደካማ ነው። ከዚህ አንጻር አዲስ ዘመን የነበረበትን እጥረት ማንም የሚያውቀው ነው። ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ ግን አዲስ

ዘመን እያወጣቸው ያሉ ዘገባዎችና ጥልቅ ትንታኔዎች በግሌ አስገርመውኛል። እንዲያውም "ጋዜጣውም በጥልቀት ታደሰ እንዴ" ስል ከወዳጄ ጋር አምተናችኋል። ለማንኛውም ጋዜጣው የጀመረው መንገድ ተገቢና አዋጭም ነውና ቀጥሉበት።

ወደ አቦይ ልመለስ።

አቦይ ስብሀት በተለያዩ ጋዜጦችና ሬዲዮኖች ላይ እየቀረቡ ይናገሯቸውና ይጽፏቸው የነበሩ አመለካከቶቻቸው ሁሌም ከሚያስደምሟቸው ሰዎች መካከል አንዱ እኔ ነኝ። የራሳቸውን ስርዓት ራሳቸው በአደባባይ የሚተቹ ብቸኛ ኢህአዴግም ሳይሆኑ አይቀሩም። ሌላው ፖለቲከኛ በቃላት አስውቦ በፖለቲካ ድባብ ሆኖ የሚናገረውን ችግር እርሳቸው እንዳለ የሚናገሩ የዚያ ዘመንም ብቻ ሳይሆን የዚህ ዘመንም ጭምር በሳል ፖለቲከኛ ናቸው። በዚህ ደረጃ ኢህአዴግ ሌሎች ሰዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ አምናለሁ። ነገር ግን መኖራቸውን የሚያውቀው ራሱ ኢህአዴግ ብቻ ነው። ምክንያቱም እንደ አቦይ አደባባይ ወጥቶ ሲጽፍና ሲናገር ሚዲያም ሳይመርጥ ሀሳቡን ሲያንጸባርቅ ያየነው ሰው እስካሁን የለም።

አቦይ እኮ ነፍሷን ይማረውና «ፍትህ» ትባል በነበረችው የግል ጋዜጣ ላይ ሳይቀር የሚጽፉ ሰው ናቸው። እንዲያውም በአንድ ወቅት ለፍትህ ጋዜጣ የላኩትን  አርቲክል አዘጋጁ እርሳቸው በላኩት ሳይሆን እሱ በፈለገው መንገድ ኤዲት አድርጎና ቆራርጦ አውጥቶባቸው ያንኑ አርቲክል ህገ መንግስታዊ መብቴን ተጋፍቶብኛል በሚል በሌላ የግል ጋዜጣ ላይ ማውጣታቸወን አልረሳውም። በተለያዩ ጋዜጦች ላይም ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር የነበራቸው የሃሰብ ፍትጊያም የሚዘነጋ አይደለም።

በዚህ ደረጃ እናውቃቸው የነበሩት አቦይ ከሚዲያ ርቀው በነበሩበት ወቅት አዲስ ዘመን ያውም በወሳኝ ወቅት ይዟቸው ብቅ ማለቱ እጅግ አስደስቶኛል። አቦይ ዛሬም እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ ያመኑበትንና መሆን ያለበትን ተናግረዋል። የሚሰማም ካለ አሳስበዋል። ኢህአዴግ ችግር ውስጥ የገባው በራሱ በኢህአዴግ እንደሆነ የተናገሩት ከስረ መሰረቱ በመነሳትና መፍትሄውንም በማመላከት ነበር። የኢህአዴግ ጉባኤ አሰራር ትክክል አይደለምና ይስተካከል ብለው አማራጭም አቅርበዋል። እኔ እንደሚገባኝ እስካሁን በዚህ ደረጃ ኢህአዴግ ችግር አለብኝ ሲል አልሰማሁም። ስለሆነም በዚህ አካባቢ መፈተሽ ያለበት ነገር እንዳለ አቦይ ያሳሰቡትን ሃሳብ እኔም እጋራዋለሁ።

በተጨማሪም አቦይ በኢህአዴግ በተለይም በብሄራዊ ድርጅቶች ዘንድ ያለውን አድርባይነት አፍረጥርጠው ተናግረውታል። ያለመነካካቱ የት ድረስ እንደሄደም ነግረውናል። ዛሬ ለገባንበት ችግርም መሰረቱ ይሄው የአመራሮቹ አለመነካካትና ችግሮችን በሌላው ላይ የማሳበብ አካሄድ እንደሆነ አስታውቀዋል።

ልብ ይበሉ፤ ህዝቡ ከኢህአዴግ ሌላ አማራጭ የለንም፤ የልማት ጥማችንን የሚያረካልን ኢህአዴግ ነው እያለ ነው ብሎ ሪፖርት ያቀረበ ብሄራዊ ድርጅት (ኦህዴድ እና ብአዴን) በወራት ውስጥ በዚሁ ህዝብ ማዕበል የተመታው ይሄን የውሸት ሪፖርት ባቀረበ በወራት ልዩነት ነው። ይሄ ሁሉ ህዝብ አደባባይ የወጣው ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላ በተፈጠረ የመልካም አስተዳደርም ሆነ የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር ተማሮ ነው ካልተባለ በስተቀር ወትሮም ቢሆን ሪፖርቱ የውሸት እንደነበሩ አቅራቢው ያውቀዋል፤ ሪፖርቱ የቀረበለት አካልም ያውቃል። ግን ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ ወይንም እኔን እስካልነካኝ ድረስ ምን አገባኝ በሚል መንፈስ ውሸት ብሎ ደፍሮ የተናገረ የለም። አቦይ ግን ይሄንን ዘክዝከው ነግረውናል። ሰሚም ካለ አሳስበዋል።

ሌላው አቦይ ሳይደብቁ ያመኑበትን የተናገሩበትና ሲበዛ ያስደመመኝ ብሄራዊ መግባባትን በተመለከተ የጠቀሱት ነው። ከተለያዩ ሚዲያዎች አዲስ ዘመንም ጨምሮ ስለ ብሄራዊ መግባባት ብዙ ሲነገር ሰምቻለሁ፤ ተጽፎም አንብቤያለሁ። ሁሉም ስለ ብሄራዊ መግባባት የሚናገረው በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ መግባባት መፍጠር የሚል አንድምታ ያለው ነው። አቦይ ግን ቃሉም አይገባኝም ሲሉ ያመኑበትን ተናግረዋል።

አቦይ እንዳሉት ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ብሄራዊ መግባባት በሚባለው ልክ አለ ወይ? ጎንደር ላይ ያየነው አንድን ብሄር ለይቶ የማጥቃት ሙከራ፣ ደቡብ ላይ የተፈጠረው የአንድን ብሄር ተወላጆች የማባረር እርምጃ በእርግጥ ብሄራዊ መግባባት እየተፈጠረ ነው ማለት ያስችላል? ለመሆኑስ አብሮ ከመኖር ሌላ ዋና ዋና አገራዊ ጉዳይ የሚባል ሌላ ነገር ይኖር ይሆን? ልማቱ ከሆነ ልማቱ ለማንም ተብሎ ሳይሆን ሁሉም ለራሱ ሲል የሚሰራው ስለሆነ ያን ያህል ብሄራዊ መግባባትን ይጠይቃል ብዬ አላምንም። ምክንያቱም ሁሉም ከክልሉ ውጪ እየተገነባ ያለውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እየገነባ ያለው «ከክልሌ ውጣ» የተባለው ህዝብም ጭምር ነውና።

ስለሆነም ዛሬ ላይ ሆነን ብሄራዊ መግባባት ተፈጥሯል በሚል መንግስት ተዘናግቶ መስራት ያለበትን መስራት እንዳይተው ወይንም እንዳይቀንስ እሰጋለሁ። አቦይ እንዳሉት መግባባቱ በሃሳብ ሳይሆን በተግባር መሆን አለበት።ስለሆነም መግባባቱ በተግባር መሬት ላይ ወርዶ ይታይ። ምክንያቱም ያለው እውነታ መግባባት መግባባት አይሸትምና።

አቦይ ሌላም ነገር አንስተዋል። ሙሰኞች በቀጠፉትና ባጠፉት ልክ መጠየቅ አለባቸው ሊጠየቁም ይገባል የሚል። ይህ አንድ እውነት ነው። መንግስትም የሚያምነው ኢ.ህአዴግም የሚቀበለው። እዚህ ላይ ግን አቦይ ባሉት ልክ ስርዓቱ ያልተረዳው ብዬ የማምነው ሙሰኞችን አለመክሰስ አገርን ወደመበታተን ማምራቱ አይቀርም የሚለውን ነው። እርሳቸውም እንዳሉት እንደ ሌሎች የአፍሪካ አገራት ሙስና እየተፈጸመ እየተንገዳገድን እንቀጥላለን የሚለው አመለካከት እዚህ አገር አይሰራም። እንደማይሰራም በተለያዩ አጋጣሚዎች ታይቷል።

የሩቁን ትተን የአሁኑን ብንመለከት እንኳን በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ተፈጥሮ በነበረው ሁከት ከብዙው በጥቂቱ ጉዳት የደረሰባቸው አመራሮች አመራር ስለሆኑ ብቻ የተፈጸመባቸው ጥቃት አይደለም። ህዝቡን ስላስመረሩ በሙስና በመልካም አስተዳደርም ቂም ስቅል ስላሳዩት ነው (ምንም እንኳን ማንኛውም ህገ ወጥ ተግባር የሚወገዝ ቢሆንም) በንብረቶቻቸው ላይ ጉዳት ያደረሰባቸው። ይሄ ልብ ላለው ልብ የሚባል እውነታ ነው። ዛሬ በማንአለብኝነት የሚዘረፍ የህዝብ ሀብት ነገ መልሶ በህዝብ ላለመነጠቁና ደም ላለማፋሰሱ ምንም ዋስትና እንደሌለ መታመን አለበት።

ስለሆነም ኢ.ህአዴግ መምረጥ ካለበት ምርጫው በሙሰኛ ግለሰቦችና በአገር መካከል ያለ ነው። የኢ.ህአዴግ ምርጫ በየትኛውም መስፈርት ከአገር ውጭ **ይሆናል** ተብሎ አይታመንም። ምክንያቱም ሙሰኞችም ቢሆን የዘረፉትን የሚበሉት አገር ሲኖር ነውና። ስለሆነም ኢ.ህአዴግ አሁን በጀመረው ልክ ራሱን ማጥራትና ወደነበረበት ከፍታ መመለስ ይጠበቅበታል። አቦይ እንደተናገሩት ይሄንን ማድረግ ሲችል ብቻ ነው ወደ ነበረበት ብቻ ሳይሆን በታሪኩ ወዳልነበረበትም ደረጃ ሊደርስ የሚችለው።

ከሙስና ጋር በተያያዘ ከአቦይ ሀሳብ ጋር የማልስማማበት ነጥብ አለ። ይሄውም ሙስና የአንድ ዘመን ክስተት አይደለም። ስለሆነም አቦይ በፓርቲው ውስጥ ኃላፊነት ላይ በነበሩበት

ዘመንም ሙስናና ሙሰኞችም ነበሩ ማለት ነው። ያን ጊዜ አሁን ባለው ልክ ወይንም አሁን ሊወሰድ በታሰበውና እየተወሰደም ባለው መጠን እርምጃ ቢወሰድ ኖሮ ዛሬ ቢያንስ የሙስና መጠን አሁን ካለው እጅግ የቀነሰ ይሆን ነበር። ቀደም ብለው በሙስና ተጠርጠረው ወደ ማረሚያ የተላኩት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች "ስርዓቱ ሳይስተካከል ነው የሄዱት" ያሉት አቦይ ስርዓቱን ማስተካከል ያልተቻለበትን አጋጣሚ ቢነግሩን ኖሮ ጥሩ ይሆን ነበር። በዚያ ደረጃ እንኳን እርምጃ ተወስዶ ሙስና ይበልጥ ነገሰ እንጂ አልከሰመም።

ለማንኛውም ግን አቦይ አሁን ያለውን ኢ.ህአዴግ ቀደም ካለው ኢ.ህአዴግ ጋር አነጻጽረው አደጋ ያሉትንም ጨምረው ያቀረቡትንና የሰጡትን ትንታኔ ልብ ለሚለው ሁሉ ትልቅ ቁምነገር ያለው ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ስለሆነም አቦይ በዚህ ብቻ ሳይገደቡ እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ አሁንም በተደጋጋሚ በሚዲያዎቻችን ብቅ እያሉ ድፍረት የሞላበትን እና ይሉኝታ ያልተጣባውን ሃሳባቸውንና አስተያየታቸውን ይነግሩን ዘንድ ምኞቴ ነው። እረጅም እድሜም መመኘቴን አድርሱልኝ።